Washington State Department of Labor & Industries

Ethiopian Community in Seattle

የሠራተኞች ካሳ (Workers' Compensation) ምንድን ነው? ለንግድ ድርጅትዎስ ለምን ያስፈልጋል?

መግቢያ

በዋሽንግተን ስቴት (Washington State) ውስጥ አነስተኛ የንግድ ድርጅት ካለዎት እና ሰራተኞችን ቀጥረው የሚያሰሩ ከሆነ፤ በሠራተኛ እና ኢንዱስትሪ መምሪያ (L&I) በኩል የሠራተኞች ካሳ መድን (workers' compensation insurance) የማቅረብ ግዴታ አለቦዎት።

1. የሠራተኞች ካሳ ምንድን ነው?

የሠራተኞች ካሳ (Workers' compensation) በሥራ ቦታ ላይ አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ ሠራተኞችንም ሆነ አሰሪዎችን ለመጠበቅ የሚረዳ የመድን (ኢንሹራንስ) ዓይነት ነው።

ይህ መድን የሚከተሉትን ይሰጣል፦

- በሥራ ላይ ጉዳት ለደረሰባቸው ሠራተኞች የሕክምና እንክብካቤ
- ሠራተኛው በሚያገግምበት ጊዜ የሚከፈል የደሞዝ ምትክ
- ለረጅም ጊዜ ለሚቆይ የአካል ጉዳት የሚሰጥ ድጋፍ (አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ)

በተመሳሳይ ጊዜ፣ አሰሪዎች እነዚህን ወጪዎች በቀጥታ ከኪሳቸው እንዳይከፍሉ ጥበቃ ያደርግላቸዋል።

2. የሠራተኞች ካሳ የሚያስፈልገው ለማን ነው?

በዋሽንግተን ስቴት ውስጥ የሚገኙ አብዛኛዎቹ የንግድ ድርጅቶች ሰራተኞች ካሏቸው የሠራተኞች ካሳ መድን ሊኖራቸው ይገባል።

ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

- የሙሉ ጊዜ ሰራተኞች
- የትርፍ ጊዜ ሰራተኞች
- የጊዜያዊ ወይም የወቅታዊ ስራ ሰራተኞች
- በድርጅቱ ውስጥ የሚሰሩ የቤተሰብ አባላት

ምንም እንኳን የንግድ ድርጅትዎ አነስተኛ ቢሆንም፣ በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች የመድን ዋስትና የመስጠት ኃላፊነት ይኖርብዎታል።

3. የሠራተኞች ካሳ ለምን አስፈላጊ ሆነ?

የሠራተኞች ካሳ የሚከተሉትን ጥቅሞች ይሰጣል፦

✓ ሠራተኞችን ለመጠበቅ

- ጉዳት ቢደርስባቸው ተገቢውን ሕክምና እንዲያገኙ ያረጋግጣል
- የገንዘብ ድጋፍ (ደመወዝ) እንዲያገኙ ያደርጋል

✓ አሰሪዎችን ለመጠበቅ

- የገንዘብ ኪሳራ ስጋትን ይቀንሳል
- ከፍተኛ ወጪ የሚያስወጡ የሕግ ክሶችን ይከላከላል

✓ የንግድ ድርጅትዎ የሕግ ግዴታውን እንዲወጣ ለማድረግ

- በሕግ የተደነገገ ግዴታ ነው
- ከመቀጫ እና ከገንዘብ ቅጣት ለመዳን ይረዳል

4. አሰሪዎች ምን ማድረግ ይኖርባቸዋል?

እንደ አንድ የንግድ ድርጅት ባለቤት፣ የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርብዎታል፡-

- ድርጅትዎን በሠራተኛ እና ኢንዱስትሪ መምሪያ (L&I) ማስመዝገብ
- ሠራተኞች የሠሩበትን የሥራ ሰዓት ሪፖርት ማድረግ
- የመድን (ኢንሹራንስ) ክፍያዎችን በወቅቱ መክፈል
- ትክክለኛ የሠራተኛ መዝገቦችን መያዝ

እነዚህ እርምጃዎች የንግድ ድርጅትዎ የሕግ ግዴታውን እንዲወጣ እና ጥበቃ እንዲያገኝ ይረዳሉ።

5. ሠራተኛ አደጋ ቢደርስበት ምን ይከሰታል?

አንድ ሠራተኛ አደጋ ቢደርስበት የሚከተሉት ቅደም ተከተሎች ይከናወናሉ፡-

1. ሠራተኛው የሕክምና እርዳታ ያገኛል
2. ለሠራተኛ እና ኢንዱስትሪ መምሪያ (L&I) ሪፖርት ይቀርባል
3. መምሪያው (L&I) የቀረበውን የካሳ ጥያቄ ይመረምራል
4. የጥቅማጥቅም ክፍያ ሊፈቀድ ይችላል

እንደ አንድ አሰሪ የሚከተሉትን በማድረግ ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡-

- ትክክለኛ መረጃ በመስጠት
- ሠራተኛው ወደ ሥራው እንዲመለስ ድጋፍ በማድረግ

ሊወገዱ የሚገቡ የተለመዱ ስህተቶች

ብዙ አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች የሚከተሉትን ስህተቶች ይሠራሉ፡-

- ለሠራተኞች ካሳ መድን አለመመዝገብ
- የሠራተኞችን የሥራ ዓይነት በትክክል አለመመደብ (Misclassifying workers)
- የሥራ ሰዓትን በትክክል ሪፖርት አለማድረግ
- የመድን ክፍያዎችን ማሳለፍ (አለመክፈል)

እነዚህን ስህተቶች ማስወገድ የድርጅትዎን ጊዜ እና ገንዘብ ሊቆጥብ ይችላል።

ማጠቃለያ

በዋሽንግተን ስቴት (Washington State) ውስጥ የንግድ ሥራ ለማካሄድ የሠራተኞች ካሳ መድን (Workers' compensation) አስፈላጊ አካል ነው። ይህ መድን ሠራተኞችዎን ይጠብቃል፣ የንግድ ድርጅትዎን ከኪሳራ ይከላከላል፣ እንዲሁም የሕግ ግዴታዎን መወጣትዎን ያረጋግጣል። መሠረታዊ የሆኑትን ነጥቦች መረዳትዎ ችግሮችን ለማስወገድ እና የንግድ ሥራዎን በልበ ሙሉነት ለመምራት ይረዳዎታል።

ዋቢ መረጃዎች (References materials)

L&I – **Employers' Guide to Workers' Compensation Insurance in Washington State**

ጠቃሚ የመረጃ ምንጮች (Resources)

ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት፡-

- ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡- https://lni.wa.gov
- **የ L&I ነፃ ተቋራጮች መመሪያን (Independent Contractor Guide)**

ይመልከቱ፦ በዋሽንግተን ስቴት ውስጥ ነፃ ተቋራጮችን ለመቅጠር የሚረዳውን የደረጃ በደረጃ መመሪያ በድረ-ገጽ Lni.wa.gov/go/F101-063-000 ያገኛሉ፤ ወይም የ L&I የአሰሪዎች አገልግሎት የእገዛ መስመርን በስልክ ቁጥር **360-902-4817** ያግኙ።

- ወደ ሠራተኞች ካሳ (workers' compensation web page) ድረ-ገጻችን መሄድ ይችላሉ፤ ወይም በስልክ ቁጥር **360-902-5775** በመደወል አሊያም ለ L&I የኢሜይል መልዕክት በመላክ ያግኙ።
- ድረ-ገጽ ይጎብኙ፦ L&I- Workers' Compensation
- ድረ-ገጽ ይጎብኙ፦ ecseattle/socialmedia